የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክት ማበልጸግ፣ ክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር ……/2019

መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 94/2019 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (13) መሠረት፤ ለፋይናንስ ቢሮ ከተሰጡ ስልጣንና ኃላፊነቶች መካከል መንግስታዊ ያልሆኑ (የሲቪል ማህበረሰብ) ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶችን ተቀብሎ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያበለጽጋል፤ ያፀድቃል፤ ውል ይፈራረማል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል በማለት ደንግ□ል፤

ቢሮው እነዚህን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክቶች በሕግ አግባብና ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣንና ተግባር በሕግ የተሰጠው በመሆኑ፤ ይህንኑ ተግባር በዝርዝር ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በአዋጅ ቁጥር 94/2019 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (13) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፕሮጀክት ማበልጸግ፣ ክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር ……/2019 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. አውጪው አካል

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 94/2019 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (13) መሠረት በፋይናንስ ቢሮ ተዘጋጅቶ የወጣ መመሪያ ነው።

3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 94/2019 ነው።
2. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ነው።
3. **"ተፈራራሚ አካላት"** ማለት የከተማ አስተዳደሩ የፖሊሲ አቅጣጫ የሚሰጥበት፣ ሕግና ስታንዳርድ የሚያወጣበት፣ አዳዲስ አሠራሮችን የሚያስተዋውቅ እንዲሁም ፕሮጀክቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን የሚከታተልና የሚቆጣጠር የዘርፍ መሥሪያ ቤት ነው።
4. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው።
5. **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው።
6. **"ክፍለ ከተማ"** ማለት በከተማው ቻርተር መሠረት የተቋቋመ የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው።
7. **"ፕሮጀክት"** ማለት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለፋይናንስ ቢሮ እና ለሚመለከታቸው የከተማ አስተዳደሩ ተፈራራሚ አካላት አቅርበው ውጤታማነቱ ተገምግሞ የፀደቀ፣ በተገደበ ጊዜ ውስጥ የሚተገበርና በጀት የተያዘለት ሥራ ነው።
8. **"አስተዳደራዊ ወጪ"** ማለት ከፕሮጀክት አጠቃላይ በጀት ለደመወዝ፣ ለአበል፣ ለጥቅማ ጥቅም፣ ለእቃዎችና ለአገልግሎቶች ግዢ፣ ለጉዞ እና ለመስተንግዶ የሚወጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አስተዳደራዊ ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች ናቸው።
9. **"ዓላማ ማስፈጸሚያ ወጪ"** ማለት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ከፕሮጀክት በጀት የሚወጣ ወጪ ነው።

10. **"ጥቅማ ጥቅም"** ማለት ድርጅቱ ለሠራተኞቹ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጠው ክፍያ ወይም አገልግሎት ሆኖ ፕሮቪደንት ፈንድ፣ ቦነስ፣ ካሣ፣ የሥራ ስንብት ክፍያ እና መሰረታዊ ዋስትናዎችን ያጠቃልላል።
11. **"እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት"** ማለት ማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በፕሮጀክት ጊዜ ውስጥ በየሩብ ዓመቱ፣ በፕሮጀክት አጋማሽ እና በፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ ለፋይናንስ ቢሮና ለተፈራራሚ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች የሚያቀርበው የፋይናንሻልና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት ነው።
12. **"የመስክ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ"** ማለት በድርጅቱ በመገኘት የሥራ አፈጻጸም ከዘርፍ ተፈራራሚ ቢሮዎች፣ ከድርጅቱ አመራሮች፣ ሠራተኞች እና ከተጠቃሚዎች ጋር በመነጋገር መረጃ በመሰብሰብ የሚከናወን ክትትልና ድጋፍ ነው።
13. **"ቁጥጥር"** ማለት ፕሮጀክቶች ሕግና ደንብን ተከትሎ መከናወናቸውን ቢሮው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ የሚያረጋግጥበት እና ከሕግ ውጪ የተከናወኑ ካሉ አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድበት ሥርዓት ነው።
14. **"የዘርፍ አስተዳደሪ"** ማለት ተገቢውን ሙያዊ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር የሚያደርግ መንግስታዊ መስሪያ ቤት ማለት ነው።
15. **"የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት"** ማለት በፈቃደኝነት የሚመሠረት፣ መንግስታዊ ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ድርጅት ያልወገነ እና ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ነው።
16. በአዋጁ ላይ የተቀመጡ ሌሎች ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
17. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ማህበራት) ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

5. መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት

የከተማ አስተዳደሩን የልማት ክፍተት የሚሞሉ የፕሮጀክት ሐሳቦች በልማታዊ አስተሳሰብ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ፣ ውስን የህዝብና የመንግስት ሃብት ለታለመለት አላማ እንዲውል

ለማድረግ፣ እንዲሁም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ከለጋሾች የሚገኘውን ሃብት ድህነት ተኮር ለሆኑ ተግባራት ብቻ እንዲውል በማድረግ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ይህንን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል።

6. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1. **የስምምነት ተገዢነትን ማረጋገጥ፡-** ድርጅቶች የፕሮጀክት ሥራቸውን በገቡት ውል መሠረት ማከናወናቸውን በማረጋገጥ ለተሻለ ውጤት ማብቃት፤
2. **ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፡-** የሕዝብና የለጋሾች ሀብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ፤
3. **የማስተካከያ እርምጃዎችን መተግበር፡-** ከሕግና ከስምምነት ውጪ የሆኑ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ፤
4. **ወጥነት ያለው አሠራር መዘርጋት፡-** በክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሥራዎች ላይ ወጥነት ያለውና ተገማች ሥርዓት መዘርጋት፤
5. **የፕሮጀክቶችን ዘላቂነት ማሳደግ፡-** አገልግሎቱ ጥራቱን የጠበቀና ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላም ዘላቂ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ፤
6. **የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት፡-** ከሀገር ውስጥና ከውጭ የሚገኝ ሀብት ብክነት በሌለበት ሁኔታ ለድህነት ቅነሳ እንዲውል ማድረግ ናቸው።

ክፍል ሁለት

ስለ ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ቁጥጥር

1. መርሆች

1. **በመረጃ ላይ የተመሠረተ አሠራር፡-** ክትትልና ቁጥጥር የሚከናወነው ድርጅቶች በሚያቀርቧቸው የሩብ ዓመት፣ የዓመት፣ የፕሮጀክት አጋማሽና ማጠቃለያ የሥራ እንቅስቃሴና የኦዲት ሪፖርቶች ላይ ተመስርቶ ይሆናል።
2. **ሁለንተናዊ የመረጃ ምንጭ፡-** መረጃዎች ከድርጅቱ ሰነዶች በተጨማሪ ከመንግሥት አካላት፣ ከለጋሾችና ከሌሎች ሦስተኛ ወገኖች በሚገኙ ሕጋዊ መረጃዎች ይደገፋሉ።
3. **የተቀናጀ የመስክ ምልከታ፡-** ቢሮው ከተፈራራሚ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት በሥራ ቦታ በመገኘት ወጥ የሆነ የክትትል ሥርዓት ይከተላል።
4. **ፍትሐዊነትና ግልጽነት፡-** አሠራሩ ግልጽነትን፣ ተገማችነትና ተጠያቂነትን የተላበሰ ይሆናል።
5. **በውጤት ላይ ያተኮረ ድጋፍ፡-** ክትትልና ግምገማ ድርጅቱን ለመገደብ ሳይሆን፣ ክፍተቶችን በውይይትና በቴክኒክ ድጋፍ በማረም ውጤታማነትን ለማሳደግ ያለመ ነው።
6. **የጥቅም ግጭትን መከላከል፡-** በክትትልና ግምገማ ላይ የሚሳተፉ አካላት ከሚገመገመው ድርጅት ጋር የጥቅም ግጭት ሊኖራቸው አይገባም።

2. ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ጉዳዮች

2.1 ክትትል እና ድጋፍ

ሀ) የሪፖርት መሠረት፡- ቢሮው ድርጅቶች በሚያቀርቧቸው የፋይናንሻልና የፊዚካል ሪፖርቶች መሠረት በዴስክና በመስክ ምልከታ ድጋፍ ያደርጋል።

ለ) የዕቅድ ዝግጅት፡- በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ወጥ የሆነ የክትትል ዕቅድና የጊዜ ሰሌዳ ይዘጋጃል።

ሐ) የክፍተቶች ልየታና ድጋፍ፡- አፈጻጸሙ ከቀረቀ ወይም ከስምምነት ውጪ የሆነ አሠራር ከታየ ተገቢው የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል።

መ) የግብረ-መልስ አሰጣጥ፡- ከክትትልና ድጋፍ በኋላ የታዩ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን የያዘ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ድርጅቱ ማስተካከያ እንዲያደርግ በ 10 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ይገለጻል።

2.2 አጋማሽና የማጠቃለያ ግምገማ

ቢሮው ፕሮጀክቱ ግማሽ የትግበራ ጊዜ ላይ ሲደርስ የአጋማሽ ክንውን ግምገማ እና ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የማጠቃለያ የውጤት ሪፖርት ከከተማ አስተዳደሩ ተፈራራሚ አካላት ጋር በጋራ ያዘጋጃል። በግምገማ ውጤቱ መሠረት ፕሮጀክቱ እንዲቀጥል፣ እንዲሻሻል ወይም እንዲቋረጥ ውሳኔ ይሰጥበታል።

2.3 ቁጥጥር

ቢሮው ድርጅቶች የፕሮጀክት ተግባራቸውን በሕግና በተቋቋሙበት ዓላማ መሠረት ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል፤ ከሕግ ውጪ የተገኙ አሠራሮች ሲታዩም ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

ክፍል ሦስት

የፋይናንስ ቢሮ፣ የዘርፍ ቢሮዎችና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የፋይናንስ ቢሮ እና የዘርፍ ቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት

1. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው ሲገኙ የፕሮጀክት ውላቸውን ከሚመለከታቸው ተፈራራሚ አካላት ጋር እንዲፈራረሙ ያመቻቻል፤
2. ለመጀመሪያ ጊዜ ፕሮጀክት ለመፈራረም ለሚመጡ ድርጅቶች የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች፡- የሕጋዊ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የፕሮጀክት እቅድ፣ ጠቅላላ የፕሮጀክት በጀቱን 10 በመቶ (10%) የሚያሳይ የባንክ መግለጫ (Statement) ወይም ከለጋሽ ድርጅቶች የተሰጠ የፋይናንስ ማረጋገጫ ደብዳቤ/የመግባቢያ ስምምነት/ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤
3. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸውን የፕሮጀክት ሰነዶች ተቀብሎ ከዘርፍ ቢሮዎች ጋር በመገምገም ያበለጽጋል፣ ውል ይፈራረማል፤

4. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በባንክ የሚያቀርቡት ጠቅላላ የፕሮጀክት በጀት ከ 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ብር በላይ ከሆነ በከተማ ደረጃ ከፋይናንስ ቢሮና ከዘርፍ ቢሮዎች ጋር ስምምነት ይፈረማል፤
5. የበጀቱ መጠን 10,000,000 (አስር ሚሊዮን) ብር እና በታች ከሆነ በክፍለ ከተማ ደረጃ ከፋይናንስ ጽ/ቤትና ከዘርፍ ጽ/ቤቶች ጋር የሚፈረም ይሆናል፤ ሆኖም ፕሮጀክቱ ከአንድ ክፍለ ከተማ በላይ የሚተገበር ከሆነ በከተማ ደረጃ የሚፈረም ይሆናል፤
6. የልማት ተግባራትና ሀብት በክፍለ ከተማ አስተዳደሮች መካከል በፍትሃዊነት መዳረሳቸውን ለማረጋገጥ ሲባል፣ የአንድ ፕሮጀክት የውል ስምምነት ቆይታ ጊዜ ከ6 (ስድስት) ዓመት መብለጥ የለበትም። ሆኖም እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ፣ ፋይዳ እና እንደ ችግሩ ጥልቀት ታይቶ የስምምነት ዘመኑ በጋራ ስምምነት ሊራዘም ይችላል።
7. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተወሰነ አካባቢ የ6 (ስድስት) ዓመት የልማት ድጋፍ አከናውነው የፕሮጀክቱ ዘመን ሲያበቃ፣ የፋይናንስ ቢሮ ከድርጅቶቹና ከሚመለከታቸው ተፈራራሚ አካላት ጋር በመመካከር፣ ተመሳሳይ የልማት እገዛ
8. የፕሮጀክቱ ተፈጥሯዊ ባህሪ እና የሚፈታው ችግር ጥልቀት የስራ ዘመኑን ከስድስት (6) ዓመት በላይ ማራዘም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ከሚመለከታቸው ተፈራራሚ የዘርፍ ቢሮዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገርና በመስማማት የስራ ዘመኑ ሊራዘም ይችላል።
9. በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ብቻ የሚካሄዱና እንደ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት እና የስልጠና ማዕከላትን የመሳሰሉ ቀጣይነትና የረጅም ጊዜ መርሃ-ግብር የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች፣ የስራ ዘመንና የቆይታ ገደባቸው እንደ አስፈላጊነቱ በፕሮጀክት ውል ስምምነቱ ውስጥ ታይቶ በልዩ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል።
10. ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የሚደረግ የአንድ ፕሮጀክት የአንድ ዙር ውል ስምምነት ቆይታ ጊዜ ከ3 (ሦስት) ዓመት መብለጥ የለበትም። ሆኖም እንደየተወጠነው ፕሮጀክት ባህሪ፣ ለከተማው ባለው ፋይዳ እና እንደ ችግሩ ስፋት ታይቶ ትክክለኛው የቆይታ ጊዜ በውሉ ላይ የሚወሰን ይሆናል።
11. የፋይናንስ ቢሮ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የቀረበለትን የፕሮጀክት ረቂቅ ሐሳብ በደረሰው በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ አስተያየት ለድርጅቱ በመስጠት ለሚመለከታቸው ሴክተር ቢሮዎች መላክ አለበት። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱም በሴክተር ቢሮዎች የተሰጡትን ማሻሻያዎችና አስተያየቶች በሰነዱ ላይ

አስተካክሎና አስጸድቆ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ለፋይናንስ ቢሮ በማቅረብ የፕሮጀክት ውል ስምምነቱን መፈራረም ይኖርበታል።

12. የፋይናንስ ቢሮ ከሚመለከታቸው ተፈራራሚ የዘርፍ ቢሮዎች ጋር በመሆን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የገቡትን የፕሮጀክት ስምምነት ጥሰው ሲገኙ ወይም ሕጋዊ ካልሆኑ ተግባራት ጋር ሲሳተፉ አስፈላጊውን የማስተካከያ ወይም የውል ማቋረጥ እርምጃ የመውሰድ፣ እንዲሁም ውሳኔውን ለሚመለከታቸው አካላት በይፋ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት።

13. የፋይናንስ ቢሮ እና የዘርፍ ቢሮዎች በክትትልና ግምገማ ወቅት የሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶችን መሠረት በማድረግ፣ ድርጅቶች የፕሮጀክት ቀረጻ፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና የትግበራ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ቀጣይነት ያለው ሙያዊና ቴክኒክ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

ለ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. ማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚንቀሳቀስ፤ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማቅረቢያ፣ የፕሮጀክት ማሻሻያ ጥያቄ፣ የክትትልና ድጋፍ ግብረ-መልስ እንዲሁም የፕሮጀክት ማጠቃለያ ግምገማ ሰነዶቹን ከፋይናንስ ቢሮ እና ከሚመለከታቸው ተፈራራሚ የዘርፍ መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን በተዘጋጁት ወጥ የሆኑ መደበኛ ፎርሞች መሠረት የማዘጋጀት እና የማቅረብ አለባቸው።

2. ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ከመተግበሩ በፊት የፕሮጀክት እቅድን ለፋይናንስ ቢሮ በማቅረብ ከሚመለከታቸው የዘርፍ ቢሮዎች ጋር በጋራ መፈራረም አለበት፤

3. በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የመረጣ መስፈርት መሰረት፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት መዋቅሮች ጋር በጋራ በመሆን ትክክለኛ የልማቱ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

4. ማንኛውም ፕሮጀክት በሚቀረጽበትና በሚተገበርበት ወቅት፣ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ባህል፣ እሴት፣ ወግና የአኗኗር ዘይቤ ያከበረና የማይቃረን መሆን ይኖርበታል።

5. ከከተማ አስተዳደሩ ለበጎ አድራጎት አገልግሎት የተሰጡ ይዞታዎችን ለንግድም ሆነ ለማንኛውም ገቢ ማስገኛ ተግባር ማዋል የተከለከለ ነው፣ ሆኖም ግን በበላይ አመራሩ ታይቶ በልዩ ሁኔታ ልፈቀድ ይችላል፤

6. የፕሮጀክቱ ፋይናንሻልና ፊዚካል የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በወቅቱ ማቅረብ አለበት፤
7. ሠራተኞቹን የደመወዝ ገቢ ግብር እንዲሁም እንደ ኪራይና ዕቃ ግዢ ያሉ ታክሶችን በአግባቡ በመሰብሰብ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ገቢ ማድረግ አለበት፤
8. የፕሮጀክቱ የሥራ ዘመን ሲያበቃ የመጨረሻውን የማጠናቀቂያ ሪፖርት ፕሮጀክቱ በተጠናቀቀበት የመጨረሻ ወር ውስጥ ማስገባት አለበት፤
9. በፕሮጀክት ስምምነት ውስጥ ያልተካተቱ ተጨማሪ ሥራዎችን ከማከናወኑ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፤ የውል ማሻሻያ የሚደረገው ከቀድሞው በጀት 10% እና ከዚያ በላይ ጭማሪ ወይም ቅነሳ ሲኖር፣ የትግበራ ቦታ ሲቀየር ወይም መሠረታዊ ለውጦች ሲኖሩ ብቻ ነው።
10. ማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የሰፈሩ የማስተካከያ ግብረ-መልሶች ወይም ግኝቶች ከፋይናንስ ቢሮ ወይም ከሚመለከተው አካል ሲደርሱት፣ በ30 (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ወስዶ ለቢሮው በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት።
11. ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ወይም ድርጅቱ ሲፈርስ ይዞታውንና ህንፃውን እንዲሁም በውል የተመለከቱ ንብረቶችን ለፋይናንስ ቢሮ ማስረከብ አለበት፤
12. ማንኛውም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለሚደረጉ የክትትል፣ የድጋፍ፣ የማረጋገጫ እና የቁጥጥር ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን፣ መረጃዎችን እና ማብራሪያዎችን ያለ ማቅማማት የማቅረብ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑን ሙሉ በሙሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

ሐ/ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የእርስ በእርስ ግንኙነት፦

1. ሊያገለግሉት ያቀዱትን ማህበረሰብ ለመደገፍ በሚደረገው ጥረት አብሮ የመስራት፣ የመተባበርና በአጋርነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።
2. የልማት አገልግሎቱን ጥራትና ተደራሽነት ለማሳደግ፤ በድርጅቶች መካከል ያለውን አቅም፣ የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጂ ሀብት፣ መረጃና መልካም ተሞክሮዎችን በጋራና በተቀናጀ መልኩ መለዋወጥ ይኖርባቸዋል።

3. የሥራ መደራረብን ለማስቀረት፣ አለማግባባቶችን በውይይት ለመፍታት እንዲሁም የዘርፉን ሙያዊ ክብር ለመጠበቅ ድርጅቶች ካልተገባ የሥራ ውድድር መቆጠብ አለባቸው።
4. የሀብት ማሰባሰብ እና የትግበራ ግልጽነት፦ ድርጅቶች በጋራ በሚሠሩባቸው የልማት መስኮች ወይም ዒላማ ማህበረሰቦች ዘንድ የሀብት ማሰባሰብ እና የፕሮጀክት ትግበራ ሥራዎቻቸው ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው መሆናቸውን በማረጋገጥ፣ ለጋራ ዓላማዎች ስኬት መተጋገዝ ይኖርባቸዋል።

5. ክፍል አራት

ሀ. የመንግሥትና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የጋራ የምክክር መድረክ

1. **የምክክር መድረክ መቋቋም፡-** በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች የዕቅድ አፈጻጸማቸውን የሚገመግሙበትና ሐሳብ የሚለዋወጡበት የጋራ የምክክር መድረክ (ፎረም) ሊያቋቁሙ ይችላሉ።
2. **አስተባባሪ ኮሚቴ፡-** መድረኩን የከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ቢሮ በበላይነት የሚመራው ሲሆን፣ ከተፈራራሚ የመንግሥት አካላትና ከሲማድ ተወካዮች የተውጣጣ አስተባባሪ ኮሚቴ እና አባላት ይኖረዋል።
3. **የበጀት ምደባ፡-** የከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ቢሮ ለመድረኩ የሚሆኑ የውይይት ሰነዶችን በማዘጋጀት፣ ጥሪ በማስተላለፍና አስፈላጊውን ማስፈጸሚያ በጀት በመመደብ ድጋፍ ያደርጋል።
4. የጋራ የምክክር መድረኩ ቢያንስ በዓመት አንዴ መደበኛ ስብሰባ የሚያደርግ ይሆናል፤ በመድረኩ የሚተላለፉ የውሳኔ ሐሳቦችና የጋራ አቅጣጫዎች በሁሉም ተሳታፊ አካላት ዘንድ ተፈጻሚ መሆናቸውን አስተባባሪ ኮሚቴው በቅርበት ይከታተላል።"

ክፍል አምስት

ሀ. የፕሮጀክቶች ዘላቂነት እና ልዩ ሁኔታዎች

1. ድርጅቶች ፕሮጀክት ሲቀርጹ ከጅምሩ የፕሮጀክቱን ዘላቂነት እና ቀጣይነት የሚያረጋግጡ ስልቶችን በግልጽ ማመልከት ይኖርባቸዋል፤

2. ከፕሮጀክት ቀረጻ እና ዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ትግበራና ክትትል ባሉት የፕሮጀክት የሕይወት ዑደቶች ሁሉ የማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎና ባለቤትነት መረጋገጥ ይኖርበታል።
3. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከአካባቢው ባህል፣ ማህበራዊ እሴት እና ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ጋር የማይጋጩ፣ በትክክል በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉ እውነተኛ ፕሮጀክቶችን የመቅረጽ ኃላፊነት አለባቸው።
4. የፕሮጀክቱን ቀጣይነት አስተማማኝ ለማድረግ፣ የአስተዳደሩ የሚመለከታቸው ቢሮዎችና ጽሕፈት ቤቶች የርክክብ ስትራቴጂውን መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብት አስቀድመው ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል።
5. የፕሮጀክት ይፋዊ ርክክብ ከመፈጸሙ በፊት ውጤቶቹን በዘላቂነት ለማስቀጠል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች መቀረጽ አለባቸው፤
6. ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ከተላለፈ በኋላም የመንግስት አስፈጻሚ አካላትና ድርጅቱ የተወሰነ ጊዜ የክትትልና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤
7. ፕሮጀክቱን ተረክበው የሚያስፈጽሙ የአካባቢው ማህበረሰብ አደረጃጀቶች ወይም የመንግስት ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አስቀድመው ሊሰጧቸው ይገባል።
8. ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ለአካባቢው ማህበረሰብ ወይም ለመንግሥት አካላት ይፋዊ ርክክብ ከተደረገ በኋላም፤ የከተማ አስተዳደሩ የሚመለከታቸው ቢሮዎች ከድርጅቱ ጋር በመቀናጀት ፕሮጀክቱ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እና ዘላቂ ጥቅም እየሰጠ መሆኑን የሚያረጋግጥ የአንድ ዓመት የድህረ-ርክክብ የክትትልና የውጤት ግምገማ ሪፖርት በጋራ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

ለ. የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ድጋፍ (ልዩ ሁኔታዎች)

1. በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለችግር የተጋለጡ ወገኖችን ለመደገፍ ሀገራዊ ጥሪ ሲኖር ወይም ከከተማ አስተዳደሩ ይፋዊ ዕውቅና ሲሰጥ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መደበኛ የፕሮጀክት ስምምነት ሳይፈራረሙ አስቸኳይ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ፤
2. እጅግ አስቸኳይ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ፣ የእርዳታ አቅርቦትና ስርጭቱ ከተጀመረ በኋላ የፕሮጀክት ስምምነቱ በሂደት ሊፈረም ይችላል፤

3. ያለ ቅድመ-ስምምነት በአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ያሰራጩትን የሀብት መጠንና የተጠቃሚዎች ዝርዝር የያዘ ይፋዊ ሪፖርት ድጋፉ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው፤
4. ድንገተኛ አደጋዎችን ለመከላከል ሲባል ድርጅቶች ቀደም ሲል ለሌላ መደበኛ ፕሮጀክት የመደቡትን በጀት ወይም ቁሳቁስ (ከተማ አስተዳደሩን አስቀድመው በማሳወቅ ወደ አስቸኳይ ጊዜ እርዳታው ማዛወር ይችላሉ።

ክፍል ስድስት

ሀ. የመጨረሻ ድንጋጌዎች

1. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ከ ...../...../2018 ዓ.ም ጀምሮ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይሆናል።

2. ተፈጻሚነት ወሰን (የቀድሞ ስምምነቶች)

ይህ መመሪያ ከመጽናቱ በፊት የተፈረመ ማንኛውም የፕሮጀክት ስምምነት ሰነድ ከዚህ ከተሻሻለው መመሪያ ድንጋጌዎችና አሠራሮች ጋር ተስማምቶ የሚመራና ለዚህ መመሪያ ተገዥ ይሆናል።